## ርእሰ አንቀፅ
## ኢትዮሚዲያ
# አየ! ይሆን ይሆን!
ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን

በ2002 ዓ ም ጠቅላይ ሚኒስትር እሆናለሁ ወይ አልሆንም ? ኒዉስ ዊክ ለመለስ ዜናዊ ከሳምንታት በፊት ያቀረበላቸዉ ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር “በ2002 የምርጫ ጊዜዎት ሲጠናቀቅ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነዉ ይቀጥላሉ?” መለስ “ምን አልባት ይህ የመጨረሻ ጊዜዬ ሳይሆን አይቀርም” ሁል ጊዚ ፈጣንና ሀይለ ቃል ያዘለ መልስ የሚሰጡት አባገነን መለስ በዚህ መልሳቸዉ ላይ ግን “ሳይሆን አይቀርም” የሚል አሻሚ ሀረግ ነዉ የተጠቀሙት” ሳይሆን አይቀርም” ምን ማለት ነዉ? በተሳቢ ግስ ቃሉን ከተጠቀሙበት “በጣም’ ’”እጅግ” ወይም “በእርግጠኝነት” የሚል ተቀፅላዎችን ያስከትላል “ይህ በእርግጠኛ የመጨረሻ ጊዜዬ ነዉ” ይህም የሀቀኝነትና የጥሩ ተማኝነትን ከጥርጣሬ ነፃ የሆነን የአንድን ሰዉ ስሜት ገላጫ አነጋገር ነዉ። እውነተኛዉ እቅድ ሳይሆን በተቀጥላነት መጠቀምን የሚያመላክት ሲሆን ደግሞ ትርጉሙ “ምን አልባት” “ሊሆን ይችላል” ስለሆነም “ምን አልባት ወይም የመጨረሻ ጊዜዬ ሊሆን ይችላል” የሚል ድብቅ መልክትን የያዘ አንደምታ ይሰጣል።

በእርግጥ ሁሉ ነገር ሊሆን ይችላል ወይም ይቻል ይሆናል ለምሳሌ ሳይንቲስቶች በመጋቢት 12 ቀን 2006 ዓ ም ከ909 000 አንዱ የሰማይ ተወርዋሪ ኮኮብ (አስትሮይድ) ከመሬት ጋር ሊላተም ይችል ይሆናል ሲሉ የመላ ምት ትንበያ ሰጥተዋል። ነገር ግን ይህ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ነዉ አስተያየቱን የሰጡት ። መለስ ስለስልጣን መውረዱን አስመልክቶ የሚለውም ምን አልባት ከ909 000 አስትሮናድ አንዱ መሬት ላይ ሊጋጭ ይችላል አይነት ነገር ነዉ። በመጨረሻዉ የሥራ ዘመኑ መዉረድ አለመዉረዱን ሊነግሩን የእርሱ መልስ አወ አይነት ይመስልና ዘወር ብሎ ግን ሀሳቤን ካልቀየርሁ ወይም ፓርቲዬ ለሌላ የምርጫ ዘመን ሀሳቤን በኀይል ጥምዝዞ እንድቀጥል ካላደረገ በስተቀር ለማለት ይሆን ይህ ዘገላለጽ፤ ወይስ አወ በእርግጠኝነት በየቀኑ ማለም ጀምር፤ ተስፋህ ህይወት እንዲኖረው አድርግ ይህ የመጨረሻ የጠቅላይ ሚኒስትነት ጊዜዬ የሚያልቅበት ይሆናል ነው የሚለውው ይህ ማለት የፕሬዚዳንትነት ስልጣን መልሼ ከመያዜ በፊት? ለማለት ይሆን። መለስ ምን ማለት እንደፈለገ አናዉቅም ወይም ማለት የፈለገዉን ይላል ማለት ነዉ።

በግንቦት 2002 መለስ ‘የጠቅላይ ሚኒስርቱነትን’ ስልጣን ይለቃል የሚል እምነት የለንም። ልክ አስትሮናይዱ ተወርዋሪወቹ የሰማይ ከዋክብት በመጋቢት 12 ቀን 2006 ዓ ም መሬት ጋር ይጋጫሉ የሚለውን እንደማናምንበት ሁሉ መለስ “በፍፁም” በፈቃደኝነት ቢሮ አይለቅም ምክንያቱም ቀላል ነዉ። መለስ በነብር ጀርባ ላይ ወጥቶ ለ17 አመት እየጋለበ ነዉ። ነብሩን መጋለብ እስከቻለ ድረስ ብቻ ነዉ መኖር የሚችለው ከጀርባ የተሸራተተ እለት ነብሩ ጋላቢ እርሱ ተገላቢ ይሆናል።

## ነብሩ

መለስና ግብረ አባሮቹ ኢትዮጵያን ከ1983 ጀምሮ እንደግል ይዞታ በመቁጠር እየመዘበሩ ነዉ። እነርሱ ወታደራዊ ገዥዉን ተክተዋል። ወታደራዊ ገዥ በ10ሺህ የሚቆጠሩትን በመግደል፤ በመግረፍና በማሰር በጨቋን አገዛዝ 17 አመት በስልጣን ላይ ቆየ። እነዚህም ይህንኑ የአደፈ ታሪክ በመድገም የደም ማፍሰስ ባህል ወረሱ።የዴማክራሲን የተቀደሰ ስም የተጭበረበረ ባንዲራ በማልበስ ካለፉት 17 አመታት እስከ አሁን ድረስ በማታለሉ ተግባር ቀጠሉ። ለምንድን ነዉ መለስ ከስልጣን መልቀቁን ጉዳይ ምን አልባት ይቻል ይሆናል የሚለዉ? ስልጣን መልቀቁ ብቻ ሳይሆ በአሳፋሪ ወንጀል ተጠያቂ መሆኑንም ያውቃል?

## ምዝበራ

መለስ በኢትዮጵያ በቅሌት ዉስጥ የተዘፈቀ የሌቦች መንግስት ይመራል። የአለቆች ሁሉ አለቃ መለስ በስርቆት ላይ የተሰማራ የአፈና ስርዓት በመዘርጋት ሀገራቱን ሀብት በመጭመቅ የራሱና የጓደኞቹ መበልጸጊያ ያደረገው ሲሆን የዉሸት ተቀጥላው ኢህአዴግን የትግራይ ወያኔ ሀርነት ግባር በበላይነት የሚጋልበው የወንጀል መፈፀሚያ ሽፋን አድርጎታል። የቀድሞዉ ፕሬዚደንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በ1994 እንዳሉት “ምዝበራ የመንግስት ተቋማት ዉስጥ ሰርስሮ የገባ ነዉ” ሲሉ ካሳታወቁ በኋላ በመቀጠልም መንግስት “ጠንካራ እርምጃ በምዝበራ ላይ መውሰድ ሲገባዉ አሁን ብኩንነት እንደ ወረርሽኝ ተዛምታል” በ1997 የኢትዮጵያ ጠቅላይ ኦዲተር አቶ ለማ አርጋዉ ባቀረበት ዘገባ “$600 ሚሊዮን ዶላር ( 6 ቢሉዮን የሚሆን የኢትዮጵያ ብር) ከክልሎች ካዝና መጥፋቱን አጋለጡ” መለስ ኦዲተር ለማ አርጋውን ከስራ አባሮ በአደባባይ የክልል ገዥዎቹን “ገንዘቡን ሊያቃጥሉትም መብት አላቸዉ” አለ “ምዝበራም የመለስ ዜናዉ ሚስጥራዊ አገዛዝ የሕይወት ደም ስር በመሆን ቀጥሏል”

## በገፍ የሰብአዊ መብት ጥስቶች

የመለስ ዜናዊ በገፍ ሰብአዊ መብቶችን መጣስ ከ1997 ምርጫ በኋላ የዓለምን ሕዝብ ትኩረት እንዲስብ አደረገ።በመለስና በፓርላማዉ የተቋቋመው የአጣሪ ኮሚሽን ዘገባ መሰረት በ1997 በሰኔና በጥቅምት ወራት ፖሊስ 193 ያልታጠቁ ሰላማዊ ሰልፈኞችን ገደለ፤ 700 የሚሆኑትን አቆሰለ፤ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ሰዎችን፤ በመቶ የሚቆጠሩ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን፤ ጋዜጠኞችና ሲቪል ማህበራት ተመራጮችን፤ የሰብአዊ መብት ታጋዮችን ያለ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እስር ቤት ተወረወሩ ሰብአዊ መብት በገፍ መጣሱ ቀጠለ።

## የሶማሌ ጦርነት እና በሰብአዊ ፍጠር ላይ የተፈፀመ ወንጀል

በሶማሊያ ላይ የተደረገዉ ወረራ በኢትዮጵያ ሕዝብ የተወደደ ተግባር አይደለም። ነጋሶ ጊዳዳ እንዳሉት “ሶማሊያ የኢትዮጵያ ስጋት አይደለችም” ሶማሌዎች እኛ ላይ ጥቃት አልፈፀሙም ስለዚህ ለምን እንወጋቸዋለን? ለኢትዮጵያዉያን ጥሩ ጥያቄ ነዉ ያቀረቡት። ለሶማሊዎች ግን ጥያቄዉ የጦርነት ወንጀልና በሰብአዊ ፍጡር ላይ የተፈፀመ ድርጊት ነዉ። ባለፈዉ ግንቦት የተመድ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አስተባባሪ ጆን ሆልመስ ሞቃዲሾን ከጎበኙ በኋላ እንደገለጡት የጦርነት ወንጀል መፈፀሙን ማጣራት ‘በግልፅ’ አሰፈላጊ ነዉ ሲሉ ሌላኛው የተመድ የሰብአዊ መብት ኮምሽነር ሊውስ አርቦር በጦርነት የተፈፀመዉ የሰብአዊ መብት ግድፈት እንደጠራ መጠያቃቸዉ ይታወሳል። በወቅቱ 1600 ሶማሊወች በጦርነቱ ሞተዋል። በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ መናገሻ ከተማውን ለቀዉ እንዲሰደዱ ተገደዋል። ከጥቂት ቀናት በፊት የመለስ ወታደሮች ቁጥራቸዉ 7-21 የሚሆኑ በመስጊድ ፀሎት ላይ የነበሩ ሰዎች ጉሮሮአቸዉን መቀረጣቸዉን አምንስቲ ኢንተርናሽናል መዘገቡ ይታወሳል። የመለስ ወታደሮች የሶማሌን ሕዝብ ማሸበራቸዉንና ማዋከባቸዉን ቀጥለዋል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል በሰላማዊ ሰዎች በመስጊድ ላይ የተፈፀመዉ ጭፍጨፋ እንዲጠራ ጠይቋል።

## በፓለቲካ መገለለል

መለስ በሀገሪቱ ፓለቲካ የተገለለና የተወገዘ ነዉ። በአማራና በኦሮሞ ተወላጆች አናሳ ድጋፍ ብቻ ነዉ ያለዉ። የወያኔ ጠንካራ ይዞታ ነዉ እያለ መለስ የሚናገርለት ትግራይ ሳይቀር አነስተኛ ድጋፍ ነዉ ያለዉ። ሕዝቡ እንደ ኢትዮጵያዊ ጨካኝ ገዥ ሳይሆን እንደ ቅጥረኛ ነዉ የሚቆጥረዉ የድሮዉ የትግራይ ገዥ የነበሩት አቶ ገብሩ አስራት እንደተናገሩት “የትግራይ ሕዝብ በምዝበራ ተቸግሯል።በመንግስት አስተዳደር እጦት ተበድሏል። መለስን የሚደግፉት ከፍራቻ በመነጨ ሁኔታ ነዉ” ብለዋል። ገብሩ አስራትና ሌሎች የወያኔ ሀርነት ትግራይ ከፍተኛ በለስልጣናት 1991-1993 ዓ ም  ከኤርትራ ጋር የተደረገዉ ጦርነት እንዲጣራ በመጠየቃቸው በ1994 ከፓርቲዉ ተባረሩ ለማስመሰያ በምዝበራና ብኩንነት ተከሰሱ።

## የአሜሪካ ድጋፍ መቀጠል?

መለስ የአሜሪካዉ ጆርጅ ቡሽ የሽብርተኛ ጣርነትን በመደገፍ ተቀጥላ ሆነ፣ በሶማሊያም የዉክልና ጦርነት ለማካሂድ ተስማማ፣ ነገር ግን የሶማሊያ ወረራ የማይወጡት ማጥ ሆነ። የሶማሊያ የእስልምና ሸንጎ ወታደራዊ ክንፍ የሆነዉ አል ሻባብ እራሱን እያጠናከረ ስለመጣ የመለሰ ወታደሮች ሊወጡ የማይችሉት ሁኒታ ተፈጠረ፣ የመለስ ደጋፊዉ ደካማዉ ጆርጅ ቡሽ ፕሬዚዳንትነት በቅርብ  ያከተማል።

መለስ ከሰኔተር ክሊተን ምርጫ ውጤት $20 ሚሊዮን ዶላር የ (የ ኢች አይቪ) የገንዘብ ድጋፍ ተስፋ አድርጓአል። ሆነም ይህ የወያኔ እቅድ በሰኔተር ኦባማ የሚደገፍ አይመስልም ።

## ለአባገነኖችና ለገዳዮች የሚሆን፡ ሀገር የለም

መለስ ለጊዜዉ ከአንዱ ወደ አንዱ መቀላወጥ ተሳክቶለታል። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ክኒንተንና የእንግሊዙ ቶኒ ቢሊር መለስን በማቆላመጥ 'የአፍሪካ የአዲሱ ትዉልዱ መሪዎች' የሚል ተቀጥላ ስም ከተሰጣቸው አንዱ ሆነ። ይህን በመጠቀም ከኢኮኖሚ ጠበብቱ ሎሬት ጆሴፍ ስቲግሊዝ ሳይቀር በማጭበርብር ይህን አስተያየት እንዲቸሩት አደረገ። "የምሁርነትና የግል ክብር አለበት፤ስለቅንነቱ ማንም አይጠራጠረውም በመንግስቱ አስተዳደር ጥቂት የምዝበራ ክሶች ይቀርቡበታል" የሚል አስተያየት ሰጡት። እንዴት ተቀለደ? በዚሁ ሙከሻ ጥቂት ጸሀይ ሳይሞቀው የአሜሪካው ኮንግሬስ ማን ክሪስ እስሚዝ( HR 2003)አስመልክቶ በተደረገ የአሜሪካው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ኮሚቴ የመረጃ ስብሰባ በተሰማበት እለት መለስንና ተከታዮቹን
"የገዳዮችና የዘረፋ ቡድን"ሲሉ ሰየሙት።

## እንድገምት አደረገኝ

የመለስ ከስልጣን መልቀቅ ንግግር ሌሎችን ለመታዘብና በተለመደው ብልጣብልጥ ዘዴው ተቃዋሚንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማዋለል የተጠቀመበት ነው።ነገር ግን ማንም አይታለልም፤ በተሻለ እናውቃለን በህይወት ለመኖር ነብሩን መጋለቡን መቀጠል አለበት።ምክንያቱን ያውቀዋል። ከወረደ ነብሩ ምልሶ እንደሚጋልበው ይገነዘባል።

በመዝገብ እንዲያዝ እኛ "በጣም ምናልባት" በሀራሬ ዚምባብዌ ከመንግስቱ ኃይለማሪያም ጋር የሚገናኝ አይመስለንም የሚል እምነት አለን፤